***በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፅድቅ***

**ለእግዚአብሔር ፍሬ በማፍራት እንኑር**

**ንባብ:-** ሮሜ 7:1-12

**ዓላማ:-**

-አማኞች ለእግዚአብሔር ፍሬ ማፍራት እንዴት እንደሚችሉ በቃሉ ማመላከት።

- አማኞች ቅዱስ ፃድቅና በጎ ፍሬን ለማፍራት ምን ማድረግ እንዳለባቸው በቃሉ ማመልከት

- አማኞች በአዲሱ የመንፈስ ኑሮ ለመግዛት እራሳቸውን መስጠት እንደሚገባቸው በቃሉ ማሳሰብ።

**መግቢያ:-** በሮሜ ምዕራፍ ስድስት በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፅድቅ በእምነት የተቀበሉ ሁሉ **በኃጢአት ላይ የበላይ መሆን የሚችሉበትን** የቃሉን እውነት ተመልክተናል ።በዛሬው ትምህርት ደግሞ ለእግዚአብሔር ፍሬ ለማፍራት እንዴት እንደምንችል የቃሉን እውነት እንመለከታለን ።

**1: ለእግዚአብሔር ፍሬ ለማፍራት ምን እናድርግ?**

1:1 በክርስቶስ ስጋ ለህግ መግደላችንን **ማመን።**

1:2 ከሙታን የተነሳው እርሱ የእኛ ባለቤት መሆኑን **ማመን።**

1:3 በአዲሱ የመንፈስ ኑሮ ለመግዛት **መፍቀድ።**

**2: ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ህጉን ማወቅ አለብን።**

2:1 ህጉ ኃጢአት አለመሆኑን **ማወቅ።**

2:2 ህጉ ለኃጢአት እንደሚያነቃን **ማወቅ።**

2:3 ህጉ ቅዱስ ትዕዛዙም ቅድስት፣ፃድቅትና በጎ እንደሆነ **ማወቅ።**

**ማጠቃለያ:-**በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፅድቅ በእምነት የተቀበሉ ሁሉ ለእግዚአብሔር ፍሬ በማፍራት ሊኖሩ ይገባቸዋል። ስለዚህ አማኝ ሁሉ በተናጠል **በክርስቶስ ስጋ ለህግ መገደሉን ማመን፣ ከሙታን የተነሳው እርሱ ክርስቶስ የእርሱ ባለቤት መሆኑን ማወቅና ማመን** እንዲሁም **ለአዲሱ የመንፈስ ኑሮ ለመግዛት መንፈስ ቅዱስን መታዘዝ አለበት።** ይህን ሲያደርግ ህጉ የሚጠይቀውን ቅድስና ጽድቅና በጎነት በማፍራት እግዚአብሔርን ማክበር ይችላል። ስለዚህ በዚህ የቃሉ እውነት መሰረት ለእግዚአብሔር ፍሬ በማፍራት እንኑር።